# የሕግ ማሻሻል



ሥዩም አርጋው

አንቀጽ _____ ምርጫ ስለማራዘም

1. በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 102 የሚቋቋመው ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ብሔራዊ ምርጫ በታቀደለት ጊዜ ማድረግ እንደማይችል ለፌደራል ሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርቦ የምርጫ ጊዜ ሰሌዳ እንዲራዘም የጠየቀ እንደሆነ የፌደራል ሚኒስትሮች ምክር ቤት ጉዳዩ በቀረበለት በሁለት ሳምንት ውስጥ ለተወካዮች ምክር ቤት ለውሳኔ በማቅረብ ፓርላማው በጉዳዩ ተወያይቶ ለአንድ ጊዜ ብቻ ከአንድ አመት ላልበለጠ ጊዜ ምርጫው እንዲራዘም ውሳኔ ሊያሳልፍ ይችላል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የቀረበው ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው በሚከተሉት አኳኋን ነው
ሀ) ረቂቅ ሃሳቡ ለፌደራል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በስልጣን ላይ ያለው መንግስት የስልጣን ዘመን ከማብቃቱ ከሦስት ወር በፊት የቀረበ እንደሆነ እና
ለ) የፌደራሉ መንግስት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምጽ የቀረበውን ሃሳብ ሲያጸድቀው

3. ገዢው መንግስት የተራዘመው ምርጫ ተደርጎ በፌደራሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አብላጭ መቀመጫ ያገኘ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ ድርጅቶች የመንግስት ስልጣን ለሚይዘው/ዙት የሚያስረክብበት ከምርጫ በኋላ ያለው አንድ ወር በአንድ አመቱ የጊዜ ገደብ ይካተታል።

4. በተራዘመው ምርጫ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አብላጫ መቀመጫ ያገኘው የፖለቲካ ድርጅት/ቶች ገዢው መንግስት ከሆነ የአምስት አመት የስልጣን ገደቡ የሚጀምረው መደበኛ ምርጫ መካሄድ ከነበረበት ጊዜ አንስቶ ሲሆን የአብላጫ ድምጽ ያገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ ድርጅቶች ከመንግስት ውጪ የሆነ/ኑ እንደሆነ የአምስት አመት የስልጣን ጊዜው/ያቸው የሚጀምረው የመንግስት ስልጣን ከተረከበበት/ቡበት ቀን አንስቶ ይሆናል።

5. በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 58(2) የተቀመጠው የምክር ቤቱ የሥራ ጊዜ ለመደበኛ ምርጫዎች የሚያገለግል ሲሆን የተራዘመ ምርጫ በተደረገ ጊዜ የመንግስት ስልጣን የሚይዘው የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ጣምራ ድርጅቶች ስልጣን የተረከበበት/ቡበት የመጀመሪያ አመት ከጀመሩበት ወር እስከ ሰኔ ያለው ሰርተው ለቀጣይ አራት ዓመት መደበኛው የህግ ድንጋጌ የሚከተል ሲሆን በመጨረሻው አመት አምስት አመት በሚሞላቸው ወር የስልጣን ገደባቸው የሚያበቃ ይሆናል።

***ሥዩም አርጋው***
06/05/2020